**ዲፓርትምንት ኦፍ ሀውሲንግ ኤንድ ኮሚዩኒቲ ደቨሎፐመንት (ዲ.ኤች.ሲ.ዲ)**

**ዲቪዥን ኦፍ ሀውሲንግ ስታብላይዜሽን (ዲ.ኤች.ኤስ)**

**ኢመርጀንሲ አሲስታንስ (ኢ.ኤ) ፕሮግራም**

**የተመሳሳይ መጠለያ ፕሮግራም ህጎች**

ህጎቹ የሚሰሩት ጃኑዋሪ 2፣ 2015 ጀምሮ ነው። መጠለያዎች የእነዚህን ተመሳሳይ ህጎች ግልባጭ እና ተግባራዊ የሚደረጉበትን ቀን የሚለጥፉ ይሆናል. **ህጎች ተጠጋግተው ለተሰሩም ሆነ በተበታተኑ ጣቢያዎች በሚገኙ መጠለያዎችና በሆቴል ምደባዎችም ተግባራዊ ይሆናሉ፣ በተለዩ ከተገለፁት ውጪ።**[1] አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑትን የተመሳሳይ መጠለያ ህጎችን ሊጥስ የሚችል አንድ ክስተት፣ ወይም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ የተመሳሳይ መጠለያ ህጎችን እና በ760 CMR 67.06 (5) (a) 3 መሰረት የተደነገገውን የቤት ባለቤት የመሆን እቅድ ጥሰት ወይም 760 CMR 67.06 (5) (a) 3. ወይም 760 CMR 67.06(6)(a)1 የሚመለከተው የጤናና የደህንነት ጥቃት እንደ አንድ የህግ ጥሰት ብቻ ይቆጠራል።[2]

***መሪ ፅንሰ-ሀሳቦች***

- የተወሰነ ግላዊነትን መጠበቅን ጨምሮ ለቤተሰቦች ሰባዊ ርህራሄና ክብር መስጠት
- የእንግዶች፣ የሰራተኛ እና የማህበረሰብ ጤናና ደህንነት
- የቤተሰቦችን ራስን ማስተዳደር ማስቀጠል እና ራስን ችሎ መኖርን/ለእራስ ብቁ መሆንን ማበረታታት
- ስኬታማ የመጠለያ አስተዳደርና የፕሮግራም ቁጥጥር

---

1 በሌላ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር፣ በዚህ ተመሳሳይ ህጎች ውስጥ ለመጠለያዎች እና ለመጠለያ ሰራተኛ የተገለፀው ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ ወይም በሆቴል ምደባዎች ለተወከሉ ወኪሎችም የሚሰራ መሆኑን ልብ ይበሉ። በዚህ የተመሳሳይ መጠለያ ፕሮግራም ህጎች፣ «ሆቴል» ሲባል ሆቴልና ሞቴልን ያጠቃልላል እንዲሁም «መጠለያ» ሲባል፣ በሌላ መልኩ በግልፅ ካልተገለፀ በስተቀር፣ ተጠጋግተው ወይም በተበታተነ ጣቢያ የሚገኙ መጠለያዎች ማለት ነው። ተባባሪ ዳይሬክተር ወይም ረዳት ዳይሬክተር የሚሉት አገላለፆች የዲ.ኤች.ኤስ ተባባሪ ዳይሬክተር እና ረዳት ዳይሬክተር ለማለት ነው።

2 አንድ ክስተት እንደ የተመሳሳይ መጠለያ ህግ ጥሰት እና በ760 CMR 67.06 (5) (a) 5. ወይም 760 CMR 67.06(a)1. መሰረት እንደ የጤናና የደህንነት ጉዳት ለመቆጠር የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ በሚላከው ህግ ያለማክበር መጠየቂያ መሰረት ሁለቱም ጥሰቶች ይታያሉ። እንደዚህ አይነት ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት፣ ክስተቱ ለጤናና ለደህንነት ጥቃት ከማድረስ ጋር የሚገናኝ መሆኑን ዲ.ኤች.ሲ.ዲ በሚገመግምበት ጊዜ ከተመሳሳይ መጠለያ ህግ ጥሰት ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም *ዲ ሚኒመስ* ወይም በቂ የመከላከያ ምክንያት መኖሩን ከግምት ውስጥ ያስገባል። አንድ ክስተት እንደ የተመሳሳይ መጠለያ ህግ ጥሰት እና በ760 CMR 67.06 (5) (a) 3. መሰረት እንደ ቤት የማግኘት እቅድ ጥሰት ለመቆጠር የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ በሚላከው ህግ ያለማክበር መጠየቂያ መሰረት ሁለቱም ጥሰቶች ይታያሉ። እንደዚህ አይነት ክስተት ሲፈጠር፣ ጥሰቱ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ህግ የሚመለከታቸው ችግሮችን፣ ለምሳሌ በተቀጠረ ስብሰባ ስላለመሳተፍ፣ አይነት ችግሮችን ያካተተ ከሆነ፣ በተጠረጠረው የድንጋጌ ጥሰት ላይ የህግ ይዘቶችም ተግባራዊ ይሆናሉ። አንድ ክስተት እንደ የተመሳሳይ መጠለያ ህግ ጥሰት እና በ760 CMR 67.06(5)(a)5. ወይም 760 CMR 67.06(6)(a)1 መሰረት እንደ የጤናና የደህንነት ጉዳት ለመቆጠር የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ በሚላከው ህግ ያለማክበር መጠየቂያ መሰረት ሁለቱም ጥሰቶች ይታያሉ እንዲሁም ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ህግ ያለማክበር ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊት ተሳታፊው ምላሽ እንዲሰጥ እድል ይሰጠዋል በተጨማሪም በማናቸውም ተያያዥ ህጎች የአሳማኝ ምክንያት ወይም *ዲ ሚኒመስ* መከላከያዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

## የዩኒቶች ተደራሽነት/ፍተሻዎች

በተጠጋጉ መጠለያዎች፣ በተበታተኑ የጣቢያ መጠለያዎች እና ሆቴሎች ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች እና/ወይም ዩኒቶች ንፅህናቸውና የጤና ወይም ደህንነት ሁኔታቸው፣ ከ24 ሰዓታት በፊት ቅድሚያ በማሳወቅ ፍተሻ ሊደረግባቸው ወይም ደግሞ የመጀመሪያው ተደጋጋሚ ፍተሻ ከመደረጉ ከ24 ሰዓታት በፊት ለኢ.ኤ ቤተሰብ እንዲያውቅ ከተደረገና ይህ ተደጋጋሚ ፍተሻ የሚደረገው ከ8፡00 በፊት ከሆነ በተደጋጋሚ ፍተሻ ሊደረግባቸው ይችላል። የፍተሻ ማስታወቂያው ከ3 ሰዓት የማይበልጥ የፍተሻ ቆይታም መጥቀስ አለት። በተጨማሪም፣ ሰራተኛ ለሁሉም የኢ.ኤ ዩኒቶች ቅድሚያ ማሳወቅ ሳይጠበቅበት የ24 ሰዓት የሆቴል ክፍሎችና የሌሎችም መዳረሻ አለው፣ (1) በአደጋ ጊዜያት፤ እና (2) የግንባታ ኮዶችን፣ የንፅህና ኮዶችን፣ የእሳት ኮዶችን ወይም የጤና ኮዶችን የመተግበር ሃላፊነት ባለባቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚደረግን ፍተሻ ለመፈፀም። አደጋዎች ሲባል የጤና አደጋዎችን እና ከፋሲሊቲዎች ጋር የተያያዙ እንደ እሳት፣ የውሃ ፍሰት እና የነፍሳት ወረራን እንዲሁም ሌሎች የአደጋ ክስተቶችን የሚያካትት ነው።

የኢ.ኤ ዩኒቶች፣ የሆቴል ክፍሎችን ጨምሮ፣ ከ24 ሰዓት በፊት በፅሁፍ ማስታዎቂያ በማሳወቅና በማስታወቂያው ለሚገለፀው እስከ 3 ሰዓት ለሚደርስ ወይም በሁለቱ ወገን በስምምነት ለተወሰነ ሰዓት ጥገና ለማከናዎን ክፍት መሆን አለባቸው። ሆቴሎች ውስጥ፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ የእራሱን ክፍል እንዲያፀዳ የተደረገ ስምምነት ኖሮ ከ24 ሰዓት በፊት በፅሁፍ በማሳወቅ የንፅህና ፍተሻ የሚደረግበት ሁኔታ ከሌለ በስተቀር፣ ለኢ.ኤ ተሳታፊዎች ቅድሚያ በተገለፀውና በሆቴሉ መግቢያ በሚገኘው ሰዓት ውስጥ ወይም በሆቴሉና በኢ.ኤ ተሳታፊዎች ስምምነት በተወሰነ ማንኛውም ሰዓሰት ውስጥ ለ3 ሰዓታት ክፍሎች በየቀኑ ለተለመደው በሆቴሉ ሰራተኞች ለሚሰራው የማስተካከል ስራ ክፍት መሆን አለባቸው። በህመም ምክንያት የክፍል ፅዳትን አለመቀበል የሚፈቀድ ሲሆን፣ በተከታታይ ከሦስት ቀናት በላይ አለመቀበል ግን አይቻልም።

በተጨማሪም፣ የመጠለያ ሰራተኛ፣ የሆቴል ሰራተኛ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ እና የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮችና ሌሎች ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር የሚሰሩ የግዛት ኤጀንሲዎች ሰራተኞች የኢ.ኤ ተሳታፊዎች የሚኖሩባቸው የሆቴል ክፍሎችን ጨምሮ ሁሉንም ዩኒቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች በተከሰቱባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ወዲያውኑ መፈተሽ ይችላሉ (1) የኢ.ኤ ቤተሰብ በጊዜው ወንጀል እየፈፀሙ እንደሆነ የሚጠቁም ምክንያታዊ፣ ሊገለፅ የሚችል ጥርጣሬ ካላቸው፤ በዚያ ጊዜ የሚያጨሱ ከሆነ፣ በማይፈቀድ እቃ በማብሰል ላይ ከሆኑ፣ ያልተፈቀደላቸው ጎብኝዎችን እያስተናገዱ ከሆነ፤ ወይም በአሁኑ ሰዓት የሌሎችን የኢ.ኤ ተሳታፊዎች ወይም የሆቴል እንግዳዎች ፀጥታ የሚያደፈርስ ወይም የተሳታፊዎችን፣ የቤተሰቡን/ቧን አባላት፣ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ የሌላ የኢ.ኤ ተሳታፊዎችን፣ በተበታተነ ጣቢያ ዩኒቶች የሚኖሩ የፎቁ ነዋሪዎችን፣ ወይም የመጠለያውን ወይም የሆቴሉን እንግዳዎች/ሰራተኞች፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኞችን፣ ወይም የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮችን እና ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር የሚሰሩ ሌሎች የግዛት ኤጀንሲዎች ሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት ስጋት ላይ በሚጥል ተግባር ላይ ከሆኑ እና (2) የተጠረጠረው ተግባር ከበር በማንኳኳትና ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር በመነጋገር ሊፈታ የማይችል ሲሆን።

አፋጣኝ መፈተሽንና የተለመዱ የሆቴል ማስተካከሎችን ጨምሮ በሁሉም መፈተሽ በተፈቀደባቸው ሁኔታዎች በሙሉ፣ የመጠለያ ሰራተኛ፣ የሆቴል ሰራተኛ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ እና የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮች ወይም ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር የሚሰሩ ሌሎች የግዛት ወይም የአካባቢ ኤጀንሲዎች ሰራተኞች በመግቢያ በር ላይ ማንኳኳት፣ የመግባት ሀሳባቸውን ማሳወቅና ከመግባታቸው በፊት ነዋሪው ቤት እንዲከፍቱ እድል መስጠት አለባቸው። በዚህ ህግ አስቸኳይ ፍተሻ ካልተፈቀደ በስተቀር፣ የመጠለያ ሰራተኛ፣ የሆቴል ሰራተኛ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ እና የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮችና የሌሎች ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር የሚሰሩ የግዛት ኤጀንሲዎች ሰራተኞች የታሰበው

ጉብኝት ማድረግ የሚችሉት ከ24 ሰዓታት በፊት በፅሁፍ ቅድሚያ በማሳወቅና ለ3 ሰዓታት ለሚቆይ ጊዜ ነው።

የልብስ ሳጥኖችን በሮች ጨምሮ፣ በሆቴሉ ወይም በመጠለያ ዩኒት የሚገኝ ማንኛውም በር በተለመዱ ፍተሻዎች ወቅት ወይም በአደጋዎች ጊዜ ሊከፈት ይችላል። በዚህ ህግ ከሚፈቀደው ውጪ፣ በልብስ ሳጥኖች ወይም መሳቢያዎች ውስጥ የተቀመጡ ንብረቶች ሊመሰቃቀሉ አይገባም እንዲሁም፣ ከማንኛውም የተፈቀደ ፍተሻ በኋላ ተስተካክለው መቀመጥ አለባቸው። በልብስ ሳጥኖች ወይም መሳቢያዎች ውስጥ የሚገኙ የግል ንብረቶች፣ ሊፈተሹ ይችላሉ፣ ነገር ግን ምክንያታዊና ሊገለፅ የሚችል ህገ-ወጥ አንቅስቃሴ፣ በእነዚህ ህጎች የተከለከለ ቁሳቁስ ወይም የተከለከለ የማሞቂያ ወይም የማብሰያ እቃ የመጠቀም ጥርጣሬ ሲኖር ብቻ። ፍተሻው ከመደረጉ በፊት መሳቢያዎች የሚፈተሹበትን ምክንያት የኢ.ኤ ቤተሰብን በፅሁፍ ሳያሳውቁ በተደረጉ ፍተሻዎች የተገኙ መረጃዎች ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ህግ ያለማክበር ወይም የማቋረጥ ክስ እንደ መረጃነት ላይወሰዱ ይችላሉ። ምክንያታዊ ጥርጣሬ በመኖሩ መሳቢያዎች የሚፈተሹ ከሆነና የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል የሚገኝ ከሆነ፣ ፍተሻው ከመደረጉ በፊት የፍለጋው ምክንያት በፅሁፍ ለቤተሰብ አባሉ የሚሰጥ ይሆናል። በእንደዚህ አይነት ፍተሻ ወቅት የቤተሰብ አባል የሌለ ከሆነ፣ ምክንያቶች በፅሁፍ ሰፍረው ከክፍሉ ውስጥ ይተዋል።

በዘህ ህግ ከተፈቀደው ውጪ፣ የመጠለያ ሰራተኞች የኢ.ኤ ቤተሰቦችን የግል ንብረቶች ሊፈትሹ አልተፈቀደላቸውም። ይሁንና፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል ወይም ጎብኚ በህገ-ወጥ እንቅስቃሴ እየተሳተፉ እንደሆነ፣ በቅጥር ግቢው ውስጥ መሳሪያ እንዳላቸው፣ ወይም ደግሞ በመጠለያው ነዋሪ ወይም ሰራተኛ ላይ የጤና ወይም የደህንነት ስጋት እንደሆኑ የሚያምኑ ስለመሆኑ ምክንያታዊ የሆነና ሊገለፅ የሚችል ጥርጣሬ ካላቸው የመጠለያ ሰራተኞች በእራሳቸው ፈቃድ ፖሊስ ሊጠሩ ይችላሉ። ከላይ የተገለፁት ሁኔታዎች በተከሰቱ ጊዜ፣ በመጠለያ ነዋሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ አስቸኳይ የጤና ወይም የደህንነት አደጋ እንዳለ ወይም የመረጃ ማጥፋት ሊፈፀም እንደተቃረበ የመጠለያ ሰራተኛ ካረጋገጠ፣ በሰዓቱ በግቢው የሚገኝ ልምድ ያለው(ላት) የመጠለያ ሰራተኛ፣ የደህንነት ስጋቱ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ከሆነ፣ ዩኒቱን እራሱ(እራሷ) ሊፈትሽ (ልትፈትሽ)፣ ወይም ዩኒቱ እንዲፈተሽ ለፖሊስ ጥቆማ ሊያደርግ (ልታደርግ) ይችላል (ትችላለች)። እንደዚህ አይነት ልምድ ያለው የመጠለያ ሰራተኛ ፍለጋው የሚከተለውን አይነት ቁሳቁስ ሊያስገኝ እንደሚችል ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ካለው ዩኒቱ በፖሊስ እንዲፈተሽ ሊጠይቅ ይችላል (1) ከባድና በፍጥነት ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ወይም ለወንጀል ተግባር ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል (የሚተኩስ መሳሪያን ይጨምራል)፣ እና (2) ቁሳቁሱ በህጋዊ መንገድ ሊገኝ የማይችል ሲሆን። ከላይ በተለገፁት ክስተቶች ውስጥ ማንኛውም ቢከሰት፣ የመጠለያ ሰራተኛ ፖሊስ ሲጠራ፣ ፖሊስ እስኪደርስ ድረስ ሰራተኞች የኢ.ኤ ቤተሰብ ዩኒቱን እንዳይደርስበት ሊገድቡ፣ እንዲሁም ፖሊስ ከደረሰ በኋላ ፖሊስ በሚጠየቀው ልክ ገደብ ሊደረግ ይችላል።

## የልጅ እንክብካቤ/የህፃናት ጥበቃ

ይህ ህግ የሚሰራው በጣቢያ ላይ ለሚደረግ የልጅ እንክብካቤ ወይም በመጠለያ ለሚደረግ የህፃን ጥበቃ ነው። ከጣቢያ ውጪ የሚደረግ የልጅ እንክብካቤ ወይም የህፃን ጥበቃ በዚህ ህግ አይሸፈንም፣ እንዲሁም ከኢ.ኤ ቤት የማግኘት እቅድ ጋር የሚጣረስ እስካልሆነ ድረስ ይፈቀዳል።

መጀመሪያ ከተመደቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት (2) ቀናት ውስጥ፣ እያንዳንዱ የኢ.ኤ ቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አንዲጠይቁ የቅፁ ቅጂ ይቀርብላቸዋል።

አንድ ጎልማሳ ወይም 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው ልጅ፣ በሆቴል ውስጥ የሚኖር ከሆነ፣ ፈቃድ በማግኘት ወይም በ760 CMR 67.06(6)(a)5 በተገለፀው መሰረት በቂ ምክንያት ሲኖር በተመሳሳይ ሆቴል ውስጥ ለሚኖር ሌላ የኢ.ኤ ቤተሰብ የህፃን ጥበቃ ሊያደርግ ይችላል።

14 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው ህፃን ፈቃድ በማግኘት ወይም በ760 CMR 67.06(6)(a)5. በተገለፀው መሰረት በቂ ምክንያት ኖሮት ለእራሱ ወይም ለታናናሽ የኢ.ኤ የቤተሰብ አባላት ጥበቃ ሊያደርግ ይችላል። ልጅ ተንከባካቢው (ወይም ለእራሱ/ሷ ጥበቃ እንዲያደርግ/እንድታደርግ ፈቃድ የተሰጠው/ጣት ልጅ) ከ16 ዓመት በታች ከሆነ/ች፣ ማንኛውም የልጅ እንክብካቤ ወይም የእራስ እንክብካቤ እንቅስቃሴ ለኢ.ኤ ቤተሰብ በተመደበ ዩኒት ውስጥ ወይም ወደ ትምህርት ቤት፣ ትምህረት ነክ እንቅስቃሴ፣ የህክምና ቀጠሮ፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር የተፈቀደ ጉዞ ወይም ሌሎች ከጤና፣ ከፀጥታና ከደህንነት ጋር የተያያዙ ቀጠሮች የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ልጅ ተንከባካቢው/ዋ ታናናሽ ልጆችን ከጣቢያው ወደ መሳፈሪያውና ከማውረጃው ወደ ጣቢያው አብሮ/ራ ሲሆን/ስትሆን ብቻ መደረግ አለበት። ልጅ ተንከባካቢው ወይም እራሱን የሚንከባከበው ህፃን ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ፣ እንክብካቤ የሚደረግለት ወይም እራሱን የሚንከባከበው ህፃን ቤተሰብ የሆነ ጎልማሳ (i) በቅጥር ግቢው ወይም የህፃኑን ድምፅ በሚሰማበት ርቀት ውስጥ ወይም (ii) በልጅ ተንከባካቢው ወይም በህፃናት በስልክ በቅፅበት ሊደረሰበት የሚችልና በአደጋ ጊዜ ወዲያውኑ ሊመልስ የሚችል መሆን አለበት።

የተፈቀዱ እቅዶች ለአንድ ጊዜ ወይም በቀጣይነት/ለረጅም ጊዜ የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከምሽሰት ገደብ በኋላ ወደ መጠለያ ለመመለስ ፈቃድ ያለው ምክንያት ከሌለ ወይም በ760 CMR 67.06 (6) (a) 5. መሰረት በቂ ምክንያት ኖሮ ካልሆነ በስተቀር በሌሊት ለሚደረግ የልጅ እንክብካቤ ፈቃድ አይሰጥም።

በመጠለያ ውስጥ፣ የልጅ ተንከባካቢ (i) በመጠለያ ሰራተኛ የተፈቀደለት/ላት (ii) በኢ.ኤ ቤተሰብ አስተዳዳሪ፣ በልጅ ተንከባካቢው/ዋ እና በመጠለያ ሰራተኛ የሚፈረም በተለመደው የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቅፅ የተፈፀመ የልጅ እንክብካቤ ስምምነት መኖርን ጨምሮ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ የልጅ እንክብካቤ መመሪያዎችን ያከበረ/ች መሆን አለበት/አለባት።

በሆቴሎች ውስጥ፣ የልጅ እንክብካቤ መጠየቂያ ቅጹን ከሆቴሉ መግቢያ በር አካባቢ ተቀብለው ይሞሉና ሆቴሉ ቅጹን ወዲያውኑ ለተወከለው አግባብነት ያለው ተባባሪ ዳይሬክተር ፋክስ ያደርገዋል (ይህን ማድረጉንም የኢ.ኤ ቤተሰቡን ያሳውቃል)፣ ተባባሪ ዳይሬክተሩም የመጠለያ ሰራተኛን በመወከል የልጅ እንክብካቤ/የህፃን ጥበቃ እቅዱን በመፈረም ያፀድቃል። የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ማንነት እና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል የሚያስፈልገው መረጃ ለሁሉም ተሳታፊዎች በሆቴሉ በር ላይ ይገኛል። የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ከሆቴሉ የመጣላቸውን የልጅ እንክብካቤ የፈቃድ ጥያቄ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ መመለስ አለባቸው። ምላሹ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ወይም ከሁለት የስራ ቀናት ቀድሞ የልጅ እንክብካቤውን ለማድረግ አስፈልጎ የልጅ እንክብካቤው ከሚደረግበት ጊዜ በፊት ካልደረሰ፣ ምላሹን በመጠበቅ ላይ ሳለ የታቀደው የልጅ እንክብካቤ ሊቀጥል የሚችል ሲሆን፣ ነገር ግን ከሁለት ቀናት ያነሰ የማስታወቂያ ጊዜ ያለው የልጅ እንክብካቤ ጥያቄ ለምን ከሁለት ቀናት በፊት አስቀድሞ እንዳልተጠየቀ አሳማኝ ምክንያት ሊኖረውና ጥያቄው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት የስራ ቀናት ክልከላ ሊደረግበት እንደሚችል መታወቅ አለበት። ቅድሚያ የተገለፀ ፈቃድ ሳይኖራቸው የልጅ እንክብካቤ የሚያደርጉ ተሳታፊዎች የተጠየቀው ላይፈቀድ እንደሚችል ግንዛቤ ይዘው መሆን አለበት። የልጅ እንክብካቤ ጥያቄዎችን በማየት ሂደት፣ በግልፅ የተቀመጠ በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ፈቃድ አይከለከልም። ሆቴል ውስጥ የሚኖሩ ተሳታፊዎች የልጅ እንክብካቤ ከሚያገኙት ቤተሰብ ጋር በአንድ ሆቴል ውስጥ የሚኖር የኢ.ኤ ተሳታፊ ልጅ ተንከባካቢ መጠቀም ይኖርባቸዋል። የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ወይም የመጠለያ ሰራተኛ የኢ.ኤ ቤተሰቡን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጤና፣ ከፀጥታ፣ ከደህንነት እና የልጆቹን አግባብነት ያለው ክትትል ከማግኘት እንዲሁም ለሌሎች የኢ.ኤ ቤተሰቦች ደርሶ ከነበረ የመረበሽ ታርክ አንፃር በበቂ ምክንያት የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቱን ላይፈቅዱ ይችላሉ። በዚህ መነሻነት የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ወይም የመጠለያ ሰራተኛው ውሳኔ በህጎች ያለፈ ህግ አክባሪነት ሊገለፅ ይችላል። ባልተፈቀደ የልጅ እንክብካቤ ወይም የህፃን ጥበቃ ምክንያት ለደረሰ ህግ አለማክበር ወይም መባረር ለሚኖር የአስተዳደራዊ ይግባኝ፣ ስልጣንን ያላግባብ መጠቀምን ማየትን ጨምሮ በM.G.L. c. 30A, § 14 (7) ለተገለፁት ምክንያቶች የዲ.ኤች.ሲ.ዲ የተጠየቀውን የልጅ እንክብካቤ ወይም የህፃን ጥበቃ ጥያቄ ያልፀደቀበት ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

በ760 CMR 67.06(6)(a)5 በተገለፁት የበቂ ምክንያቶች መስፈርቶች መሰረት በቂ ምክንያት ኖሮ ካልሆነ በስተቀር፣ የልጅ እንክብካቤ የሚፈቀደው በዚህ ህግ መሰረትና ለተፈቀደው ጊዜ ብቻ ነው። በ760 CMR 67.06(6)(a)5 መሰረት በቂ ምክንያቶች መኖራቸውን በመወሰኑ ሂደት፣ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ የልጅ(ጆች) እድሜ እና ያለ ፈቃድ የተደረገውን የልጅ እንክብካቤ የጊዜ ቆይታ፣ የልጅ እንክብካቤ ጊዜው ከተፈቀደው ጊዜ ያሳለፈውን የጊዜ ርዝመት እንዲሁም የተራዘመው የልጅ እንክብካቤ በልጅ(ጆች) ጤና፣ ፀጥታ እና ደህንነት ላይ የነበረውን ተፅዕኖ ጨምሮ ሁሉንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን፣ የልጁን(ጇን) እድሜ እና በልጁ(ጇ) ላይ ተጋርጦ የነበረ አደጋ ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

የተፈቀደላቸው የልጅ ተንከባካቢ ለልጅ(ጆች) እንክብካቤ በሚያደርጉበት ወቅት ሁሉንም የፕሮግራሙን ድንጋጌዎችና የተመሳሳይ መጠለያ ፕሮግራሙንና በዲ.ኤች.ሲ.ዲ የተመሰረቱ የሆቴል ህጎችን ማክበር አለባቸው። ልጅ(ጆች)ን በአግባቡ ባይቆጣጠሩ ወይም የልጅ(ጆች)ን ጤናና ደህንነት ባግባቡ ባይዙ፣ የልጅ(ጆች) ወላጅ በሚመለከታቸው ልክ የልጅ ተንከባካቢዎችንም የኢ.ኤ መመሪያ በእኩል ደረጃ ይመለከታቸዋል።

በተለየ መልኩ ካልተፈቀደ ወይም በ760 CMR 67.06 (6) (a) 5 በተገለፀው የበቂ ምክንያት መስፈርቶች መሰረት በቂ ምክንያት ኖሮ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የልጅ እንክብካቤ እቅድ የምሽት ገደብን በተመለከተ ህጉን ማክበር አለበት። የልጅ ወላጅ ከምሽት ገደብ በኋላ ለመመለስ ፈቃድ አግኝተው በልዩ ሁኔታዎች ያልተፈቀደ ከሆነ፣ ወይም ከላይ በተገለፀው መልኩ በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር፣ ልጅ ተንከባካቢ ከምሽት ገደብ በኋላ ወይም ከ6:00 ኤ.ኤም በፊት እንክብካቤ ማድረግ አይችሉም። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን፣ የልጁን(ጅቷን) እድሜና በልጁ(ጅቷ) ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር ጨምሮ ሁሉንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ህግ መጣስ *ዲ ሚኒምስ*(ጥቃቅን) እንደሆነ ስለሚቆጠር እንደ ህግ አለማክበር ሊቆጠር ወይም መባረር ሊያስከትል አይችለም። ከምሽት ገደብ በኋላ ወይም ከ6 ኤ.ኤም በፊት የሚደረግ የልጅ እንክብካቤ፣ ለምን ከምሽት ገደብ በኋላ ወይም ከ6 ኤ.ኤም በፊት ለማድረግ እንዳስፈለገ በመግለፅ፣ በተለመደው የዲ.ኤች.ሲ.ዲ የልጅ እንክብካቤ ስምምነት ቅፅ ላይ በግልፅ መጠየቅ አለበት።

**የልጆች እድሜ**

የኢ.ኤ ቤተሰብ ጎልማሳ አባላት እና በኢ.ኤ ቤተሰብ ውስጥ ታዳጊ የቤተሰብ አባላት በኢ.ኤ ዩኒት ውስጥ ለሚኖሩ ልጆች ጤና፣ ፀጥታና ደህንነት ሃላፊነት አለባቸው (ለምሳሌ ትምህርት ቤት መሄዳቸውን የመከታተል፣ በትክክል ምግብ መውሰዳቸውንና ረፍት ማግኘታቸው ማረጋገጥ)። የኢ.ኤ ቤተሰብ ከጣቢያው ውጪ በሆነበት ሰዓትም ለምሳሌ በተፈቀደ የውጭ ማደር ጊዜ ወይም የኢ.ኤ ቤተሰብ የምሽት ገደብን ጨምሮ በሌሎች የመጠለያ ህጎች መሰረት በተፈቀደለት ሁኔታ ውስጥ እያለም ቢሆን ይህ ሃላፊነት ፈፅሞ የቀነሰ አይሆንም። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን፣ የልጁን(ጇን) እድሜ እና በልጁ(ጇ) ላይ ተጋርጦ የነበረ አደጋ ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**ለብቻው(ዋ) የተተወ(ዎች) ልጅ**

<u>**ማስጠንቀቂያ፡- አንድ ልጅ ጥበቃ ከሚያደርግለት ጎልማሳ ወይም ከተፈቀደለት የልጅ ተንከባካቢ ለአፍታም ቢሆን ከእይታ ወይም ከድምፅ ውጪ ከሆን ወይም በአስቸኳይ ቁጥጥር ሊደረግለት ከሚችልበት ርቀት ውጪ ቢሆን ዲፓርትመንቱ ልጁ(ቷ) ብቻውን(ዋን) እንደሆነ(ነች) ይቆጥረዋል።**</u>

የእራሳቸውን የልጅ እንክብካቤ በእራሳቸው እንዲያደርጉ በልጅ እንክብካቤ ህጎች ካልተፈቀደላቸው ወይም በጎብኝዎች/እንግዳዎች ህግ ላይ በሚፈቀደው መሰረት የጋራ አካባቢዎችን ለመጎብኘት ካልሆነ ወይም በ760 CMR 67.06(6)(a)5 የበቂ ምክንያቶች ስታንዳርዶች መሰረት እንደ በቂ ምክንያት የሚቆጠር ሆኖ ካለሆነ በስተቀር በመጠለያ ወይም በሆቴል ቅጥር ውስጥ የኢ.ኤ ቤተሰብ ልጆች ለብቻቸው መሆን አይችሉም። የእራሱን(ሷን) የልጅ እንክብካቤ ለማድረግ የተፈቀደለት(ላት) ልጅ በልጅ እንክብካቤ/ የህፃን ጥበቃ ህጉ ሽፋን ማግኘት አለበት(ባት)። አንድ ተሳታፊ ልጁን ለብቻ በመተው በቂ ምክንያት እንዳለው በሚታይበት ወቅት፣ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ የልጁን(ጆችን) እድሜ እና ልጁ(ጆች) ለብቻ የቆየበትን(የቆዩበት) የጊዜ ርዝመትና ሌሎችንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን፣ የልጁን(ጇን) እድሜ እና በልጁ(ቷ) ላይ ተጋርጦ የነበረ አደጋ ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**የምሽት ገደብ**

በስራ ቀናት (ከእሁድ እስከ ሀሙስ ምሽቶች) ከ9፡00 ፒ.ኤም በፊት እንዲሁም ስራ በሌለባቸው ምሽቶች (አርብ እና ቅዳሜ ምሽት) ከ11፡00 ፒ.ኤም በፊት ሊሆኑ በማይችሉት እንዲሁም ከ11፡00 ፒ.ኤም (ከእሁድ እስከ ሀሙስ ምሽቶች) እና 1፡00 ፒ.ኤም (አርብ እና ቅዳሜ ምሽቶች) በኋላ ሊሆኑ በማይችሉት የኢ.ኤ ቤተሰብ በመጠለያ ወይም በሆቴሉ ውስጥ እንዲገኙ የሚጠየቁ የምሽት ገደቦችን ማክበር ያስፈልጋል። በምሽት ገደብ ምክንያት መጠለያዎች ፕሮግራማቸውን ወይም የምግብ እቅዳቸውን ሊቀይሩ አይገደዱም።

መጠለያ ወይም ሆቴል ከምሽት ገደብ በፊት ከአንድ ሰዓት የማይበልጥ የፀጥታ ጊዜ ሊጥል ይችላል። መጠለያው ወይም ሆቴሉ የኢ.ኤ ቤተሰብ በተፈቀደላቸው ክፍሎች መገኘት ያለባቸውን የምሽሰት ሰዓት ገደብ ሊጥል የሚችል ሲሆን ይህ ሰዓትም በግቢ ውስጥ መገኘት ካለባቸው የምሽት ገደብ ከአንድ ሰዓት በኋላ ሊሆን ይችላል። ምክንያታዊ የሆነ የጤና፣ የፀጥታና የደህንነት ፍላጎቶች ሲኖሩ፣ የኢ.ኤ ተሳታፊ በክፍል ውስጥ ለመገኘት የተቀመጠውን ገደብ ላለማክበር ከስራ አምሽቶ መመለስ ወይም ትምህርት አይነት በቂ ምክንያት ለመጠለያ ወይም ለሆቴል ሰራተኛ ለማቅረብ ከቻሉ፣ በክፍል ለመገኘት የተቀመጠውን ገደብ ላለመጠበቅ ስምምነት ሊደረግ ይችላል።

በክፈል ውስጥ የመገኘት ገደብ ከ6፡00 ኤ.ኤም በፊት ማብቃት አለባቸው።

እያንዳንዱ የምሽት ገደብ በኢ.ኤ ቤተሰብ የስራና የትምህርት ቤት ፕሮግራም ወይም በሌሎች ቤት ለማግኘት ባሉት ግዴታዎች እንዲሁም የአካል ጉዳተኝነት ለማስተናገድ ወይም ሌሎች በ760 CMR 67.06(6)(a)5. በተገለፁት በቂ ምክንያቶች መሰረት እንደሁኔታው ማስተካከያ ሊደረግበት ይችላል።

የምሽት ገደቦች ህጎች ልዩ ፈቃዶች እንደሁኔታው በስፖርት ፕሮግራሞች፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተክርስቲያን ወይም በህክምና ቀጠሮዎች፣ በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎችና በሌሎችም በቂ ምክንያቶች ብቻ በመጠለያ ወይም በሆቴል ሰራተኛ ወይም በተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ አማካኝነት ሊፈቀዱ ይችላሉ።

የምሽት ገደብን ለማስተካከል የመጠለያ ሰራተኛን ወይም ተባባሪ የዳይሬክተሮች ተወካይን መጠየቅ የሚቻል ሲሆን ሊገኙበት የሚችሉበት መረጃ በእያንዳንዱ መጠለያና ሆቴል ይገኛል። የምሽት ገደብ ማስተካከያው ከተፈለገበት ከሁለት የስራ ቀናት በፊት ከተደረገና በግልፅ ክልከላው ካልደረሰዎ፣ እንደተፈቀደ ሊቆጥሩት ይችላሉ።

የምሽት የጊዜ ገደብን ማክበር የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት ከመጠለያ ውስጥ ሃላፊነታቸውና በኢ.ኤ ቤተሰብ ውስጥ የልጆችን ጤና፣ ፀጥታና ደህንነት ለመጠበቅ ካለባቸው ሃላፊነት ሊያዘናጋቸው አይችለም።

የምሽት ገደቡ ካለፈ በኋላ መድረስ በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያት መስፈርት መሰረት ምክንያት ሊቀርብ ይችላል። ተሳታፊው የምሽት ገደብ አሳልፎ በመምጣት የሚያቀርቡትን በቂ ምክንያት በመመልከቱ ሂደት፣ የዘገዩትን መጥን፣ መዘግየትን ቀድሞ በማሳወቅ የተወሰደን ሃላፊነትን በራስ መውሰድ፣ እንዲሁም ዘግይቶ በመምጣት በልጅ(ጆች) ጤና፣ ፀጥታና ደህንነት ላይ ሊኖር የሚችለውን ችግርና የመሳሰሉትን አጠቃላይ ሁኔታዎች ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ከግምት ውስጥ ያስገባል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱንና ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳትና ወጪዎች**

የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት በመጠለያ ወይም በሆቴል ንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ወይም ለፍጆታ የሚውሉ ንብረቶችን ካልሆነ በስተቀር፣ በ760 CMR 67.06 (6) (a) 5 በተቀመጠው መሰረት በቂ ምክንያት ሳይኖር የመጠለያ ወይም የሆቴል ንብረት ሊወስዱ አይችሉም። የተለመደ ማለቅ ወይም መቀደድ እንደ ጉዳት መወሰድ የለበትም። ጉዳቱ ሆን ተብሎ፣ ባለመረጋጋት ወይም በተደጋጋሚ የተፈፀመ ካልሆነ በስተቀር፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ በአንድ አመት ውስጥ የመተኪያውን ወይም የጥገናውን ወጪ ለመመለስ ምክንያታዊ የሆነ እቅድ ያለው ከሆነና የክፍያ ጊዜውን ጠብቆ የሚከፈል ከሆነ፣ ክፍያው ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ህግ ያለማክበር ቅጣቱ በይደር መቆየት አለበት። መልሶ መክፈሉ በእቅዱ መሰረት በሙሉ ከተከፈለ፣ ህግ ያለማክበር ቅጣቱ ውድቅ ይደረጋል።

በስታንዳርድ ተጠቃሚነት በመጠለያው ወይም በሆቴሉ የማይሸፈኑ ተጨማሪ ወጪዎችን የኢ.ኤ ቤተሰብ መክፈል አለበት። ይህም ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ የተደረጉ የስልክ ወጪዎችን ወይም የፊልም ኪራዮችን ያካትታል። በሆቴል ውስጥ በክፍያ የሚስተናገድ ደንበኛ እንዲከፍል በማይጠየቅባቸው የስልክ ጥሪዎች ወይም ሌሎች ወጪዎች የኢ.ኤ ነዋሪዎች እንዲከፍሉ አይጠየቁም። መጠለያው ወይም ሆቴሉ ምንም ምን ነገሮች እንደሚያስከፍሉ አስቀድሞ የኢ.ኤ ቤተሰብን በፅሁፍ ያሳውቃል። በአደጋ ጊዜ ወይም ቤት ለማግኘት የሚያግዝን ሰራተኛ ለማግኘት ወይም በሌሊት ውጪ ለማደር ወይም የልጅ እንክብካቤ ፈቃድ ለማግኘት የመሳሰሉትን አንገብጋቢ ጉዳዮች ለመፈፀም ወደ ቢሮ ወይም ወደ ተወካይ ስልክ ለመደወል ተንቀሳቃሽ ስልክ የሌለው የኢ.ኤ ቤተሰብ ያለምንም ክፍያ እንዲደውል ሆቴሎችና መጠለያዎች ይፈቅዳሉ።

በ760 CMR 67.06(6)(a) 5 መሰረት በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ፣ በኢ.ኤ ቤተሰብ ባህሪ ለጠፋ የመጠለያ ወይም የሆቴል ንብረት ወይም ማንኛውም የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል ወይም የቤተሰብ እንግዳ ባደረሰው ከተለመደ ማለቅ ወይም መቀደድ ላለፈ ጉዳት የኢ.ኤ ቤተሰብ የሚከፍል ሆናል። ንብረቱ በተለየ ሁኔታ ቆሽሾ ወይም ንፅህናው ሳይጠበቅ ተገኝቶ ለማፅዳት የሚያስወጣውን ተጨማሪ ወጪ መሸፈንንም ያካትታል። የኢ.ኤ ቤተሰብ እነዚህን ወጪዎች ለመሸፈን ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ክፍያዎቹን መፈፀም ያለበት ሲሆን የመልሶ ክፍያ እቅዱ የቤተሰቡን ገቢና ወጪ ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሁም በኢ.ኤ ቤተሰብ ጎልማሳ አባላት የቤት ማግኘት እቅድ ውስጥ የተካተተ መሆን አለበት። ክርክር የተነሳባቸው ክፍያዎችና የክፍያ እቅዱ ምክንያታዊነት በዲ.ኤች.ሲ.ዲ የክስ ሰሚ ክፍል ለህግ ጥሰት በአስተዳደራዊ ይግባኝ የህግ አለማክበር ወይም መባረር አንድምታ ይግባኝ ሊባልባቸው የሚችሉ ናቸው። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን ወይም መጠኑን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ* (ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**አስፈላጊ ቀጠሮዎችን ጨምሮ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ መስፈርቶች**

በቤት ማግኘት እቅዱ (ማለትም መቆጥብ፣ የቤት ፍለጋ፣ ስራ ፍለጋ) ወይም ቤት የማግኘት እቅድ በሌለበት ጊዜ የ760 CMR 67.06(4)(b) መስፈርቶች ለጎልማሳ የኢ.ኤ ቤተሰብ በቃል እና በፅሁፍ ምን እንደሆኑ እና እነዚህን መስፈርቶች እንዴት ማሟላት እንደሚቻል ከተብራሩ በኋላ በመስፈርቱ መሰረት ቤት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን የዲ.ኤች.ሲ.ዲ መስፈርቶች ማሟላት የኢ.ኤ ቤተሰብ ግዴታ ነው።

በመጠለያ ሰራተኛ፣ በዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛና ለኢ.ኤ ተሳታፊዎች የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ በሚገኙ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮች የተጠሩ ሁሉንም ስብሰባዎችን የኢ.ኤ ቤተሰብ እንዲሳተፍ ይጠበቃል። የኢ.ኤ ቤተሰብ ስብሰባው ከመደረጉ ከሁለት የስራ ቀናት በፊት እንዲያውቅ የሚደረግ ሲሆን ስብሰባው ተከታታይ ከሆነ ግን የሁለት ቀን ቅድሚያ ማሳወቅ የሚያስፈልገው ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚደረገው ብቻ ይሆናል። ድንገተኛ ጉዳይ ወይም ሌላ በቂ ምክንያት ቢያጋጥም የኢ.ኤ ተሳታፊ ስብሰባ ለጠራው አካል መደወል እንዲችል የፅሁፍ ማስታወቂያው ስልክ እና ፋክስ ቁጥር ይጠቀሳል። የጉዳዩ ሰራተኛ

ስልክ ቁጥር ተሰጥቶ የነበረ ተሳታፊ ከስብሰባው ሰዓት ቢያንስ ከሁለት ሰዓታት ቀድሞ በመደወል፣ አጭር የፅሁፍ መልዕክት በመላክ ወይም የፋክስ መልዕክት በመላክ ቀጠሮ እንዲቀየርለት የጠየቀ ከሆነ ህግ እንደጣሰ ወይም ቤት የማግኘት እቅዱ የሚተዳደርበትን ህግ እንደጣሰ አይቆጠርበትም። ሰራተኛ ወይም አገልግሎት ሰጪ ከ15 ደቂቃዎች በላይ ከዘገየ፣ ተሳታፊው መጠበቁን ባለመቀጠሉ ይህን ህግ ወይም 760 CMR 67.06(5)(a)3 እንደጣሰ አይቆጠርበትም።

የኢ.ኤ ቤተሰብ በተመደበበት ቀን ምክንያታዊ በሆነ ሰዓት ውስጥ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ እንዲደርስ ይጠበቃል። የኢ.ኤ ቤተሰብ በዲ.ኤች.ሲ.ዲ ትራንስፖርቴሽን ለመንቀሳቀስ ከተስማማ፣ በቂ የሆነ ምክንያት ከሌለው በስተቀር የኢ.ኤ ቤተሰቡ ትራንስፖርት እንዲጠብቅ በተነገረው ቦታና ሰዓት መገኘት አለበት። የኢ.ኤ ቤተሰብ በራሳቸው ትራንስፖርት ከተመደቡበት ለመድረስ ከተስማሙ፣ መጠለያ አቅራቢው የተለየ ጊዜና ቦታ ካልገለፀ ወይም ሌላ በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር፣ ከአካባቢያዊ ተባባሪ ዳይሬክተር ወይም ከተወካያቸው ፈቃድ ሳይኖር ወደተጠጋጋ መጠለያ ወይም ወደሆቴል ከ8 ፒ.ኤም በፊት መድረስ ያለባቸው ሲሆን መጠለያው ከ2:00 ፒ.ኤም በፊት የተሰጣቸው ከሆነ ለተበታተነ የጣቢያ ዩኒት ወደመጠለያ አቅራቢው ቤት ከ5 ፒ.ኤም በፊት መድረስ አለባቸው። የኢ.ኤ ቤተሰብ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ በሰዓት ካልደረሰ፣ ክፍሉ ሊሰረዝ ይችላል። የምደባ ማስታወቂያዎች ወደ መጠለያው ወይም ወደ ሆቴሉ ወይም ወደ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ በመደዋል በቂ ምክንያት በመኖሩ ዘግይተው እንደሚደርሱ የሚገልፁበት ስልክ ቁጥር ሊኖረው ይገባል።

ሆቴሎች ውስጥ የተመደበ የኢ.ኤ ቤተሰብ ወደ ሆቴሉ በመደዎል ወይም በየቀኑ በ1 ፒ.ኤም ከሆቴሉ የእንግዳ መቀበያ በመቅረብ የኢ.ኤ ቤተሰቡ ወደ መጠለያ መዘዋወር እንዳለባቸው እንዲጠይቁ ወይም ማንኛውንም ዝውውር ለማሳወቅ እንዲቻል ሊገኙበት የሚችል ስልክ ቁጥር ለሆቴሉ እንዲተዉ ይጠበቃል።

ይህን ህግ ላለማክበር በቂ ምክንያት ካለ ምክንያቱ በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያቶች ስታንዳርድ መሰረት ይታያል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱንና ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**ጸጥታ መረበሽ**

በ760 CMR 67.06 (6) (a) 5. የበቂ ምክንያቶች መስፈርት መሰርት በቂ ምክንያት የሚባል ከሌለ በስተቀር የኢ.ኤ ቤተሰብ የሌሎችን የኢ.ኤ ተሳታፊዎች፣ በተበታተነ የአፓርትምንት ህንፃዎች የሚኖሩ ሌሎች ነዋሪዎችን ወይም የሌሎች የሆቴል እንግዳዎችን ፀጥታ በእጅጉ እና በተጨማጭ በሚያውኩ ምክንያታዊ ያልሆኑ ተግባራት መሳተፍ የለበትም። አንድ ተግባር ሌላ የኢ.ኤ ቤተሰብ፣ ነዋሪ ወይም እንግዳ እየረበሸ እንደሆነ ከተገለጸ በኋላ በተለየ መጠን የሚቀጥል ካልሆነ በስተቀር፣ እንደ መሳቅ፣ ማልቀስ፣ ንግግር፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ወይም ሙዚቃ ማዳመጥ፣ ስልክ ማውራት፣ በተለመደ ጨዋታ ላይ ያሉ ልጆች እንቅስቃሴ፣ ወይም አግባብ ባለው ሰዓት (የተጠቀሰ ከሆነ) ልብስ ማጠብ የመሳሰሉትን የህይወት እንቅስቃሴዎች ምክንያታዊ ያልሆኑ ተብለው አይወሰዱም። በተጠጋጋ መኖሪያ ሊኖሩ የሚጠበቁ ረብሻዎች ከፍተኛና ተጨባች ሁከት ተብለው አይወሰዱም። በምደባ ቦታው ወይም አጠገብ የመጫዎቻ ቦታ መኖሩ የልጅን ተግባር እንደ ፀጥታ መረበሽ መውሰድና አለመውሰዱ ላይ ለውጥ ተፅዕኖ አይኖረውም።

**የአደንዛዥ እፅ ምርመራ**

የሽንት ማጣራትና የደምና የትንፋሽ ምርመራን ጨምሮ የአደንዛዥ እፅ ምርመራ፣ በዘፈቀደ ወይም በጅምላ አይደረግም፤ ይሁን እና የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል ቁጥጥር የተደረገባቸውን ንጥረ-ነገሮች ያላግባብ እየተጠቀመ እንደሆነ የሚያመለክት በግለሰብ ላይ ያተኮረ ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሰራተኛ በታመነ ጊዜ የኢ.ኤ ቤተሰብ በሰራተኛ ለሚቀርበው የአደገኛ እፅ ምርመራ ጥያቄ በጎ ምላሽ መስጠት አለበት። ማንኛውም እንደዚህ አይነት ምርመራዎች የሚደረጉት በመጠለያው ወጪ ነው።

**የእሳት አደጋና ማጨስ**

በማንኛውም የመጠለያ ዩኒት ህንፃ ውስጥ ማጨስ ክልክል ነው።

ጭስ ወይም ካርቦን ሞኖ አክሳይድ ጠቋሚዎችን ወይም በውስጣቸው የሚገኘውን ባትሪ ማስወገድ ክልክል ነው።

መጠለያዎች ክፍት የማጨሻ አካባቢ(ዎች) በመሰየም ለነዋሪዎች ማሳወቅ አለባቸው። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) ከተከለለ የማጨሻ አካባቢ አኳያ የህግ ጥሰት እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

ሁሉም የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች ማጽዳት አለባቸው። በተከለለ ቦታ ከማጨስ በዘዘለ፣ የመጠለያው ሰራተኛ በግልፅ ተስማምተው ካልሆነ በስተቀር (የልደት ሻማዎች፣ በመጠለያው የቀረቡ የውጭ ፍሞች፣ ፓይለት በሌለበት ጊዜ ምድጃ ለመጠቀም)፣ እንደ ላይተሮች፣ ክብሪቶች፣ ሻማዎች፣ እጣን፣ እሳት ማውጫዎች፣ የተቀጣጠለ ጋዝ ወይም ከሰል አይነት ተቀጣጣይ ቁሳቁሶችን በመጠለያው ግቢ ውስጥ መጠቀም የተከለከለ ነው።

በመጠለያ ውስጥ፣ ትኩስ ድስቶችና ሌሎች የማብሰያ መሳሪያዎች የሚፈቀዱት በማብሰያ ቤት ወይም በመጠለያው ፈቃድ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ በመጠለያው በተወሰኑ የማብሰያ አካባቢዎች ብቻ ነው። ሆቴሎች ውስጥ፣ በሆቴሎች ካልቀረቡ በስተቀር ትኩስ ድስቶችና ሌሎች ማብሰያ መሳሪያዎች የተከለከሉ ናቸው። እነዚህን ህጎች በመቃረን በምደባ ቦታ የተገኙ ትኩስ ድስቶችና ሌሎች ማብሰያ እቃዎች የሚወረሱ ሲሆን እንደ ስነ-ምግባር ጉድለት ሊቆጠሩ የሚችሉት ግን በሆቴሉ ውስጥ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የሚያመለክት መረጃ ከተገኘ ብቻ ነው።

**የሚያስጨንቁ ወይም የዛቻ ቋንቋዎች**

ማንም የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል (1) በቃል ሊያስጨንቅ (2) ወደሌሎች ነዋሪዎች ወይም እንግዳዎች፣ አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም የዲ.ኤች.ሲ.ዲ፣ የሆቴል ወይም የመጠለያ ሰራተኛ የዛቻ ቃላትን ሊጠቀም አይችልም። የኢ.ኤ ቤተሰብ በመጠለያ ወይም በሆቴል ሰራተኛ ለተነሳበት ፀብ-አጫሪነት አግባብነት ባለው መልኩ ምላሽ በመስጠት የተፈፀመ ከሆነ ይህን ህግ ለመጣስ በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችልበት እድል አለ።

**ህገ-ወጥ እንቅስቃሴ**

በመጠለያው ቅጥር ውስጥ ወይም አቅራቢያ በአካባቢው፣ በግዛት ወይም በፌደራል ህግ መሰረት ህገ-ወጥ የሆነ ተግባር መፈፀም የተከለከለ ነው።

**ህጋዊ ጉዳዮች**

በሂደት ላይ ያለ መጥሪያ ወይም ማዘዣ ካለው ጉዳዩ የቀረበው በኮመንዌልዝም ሆነ በዲ.ኤች.ሲ.ዲ አማካኝነት የተገለፀለት፣ በቤት ማግኘት እቅዱ ውል መሰረት መፈታት ያለበትና ይህ በተገለፀ በ30 ቀናት ውስጥ መፍትሄ ያላገኘ ከሆነ፣ አንድ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል የህግ ጥሰት እንዳለበት ሊጠቀስ ይችላል።

ህጋዊ ጉዳዮችን መፍታት በቤት ማግኘት እቅዱ ውስጥ መካተት አለበት። ይህን መስፈርት በመደገፍ፣ ማዘዣዎችን፣ የክልከላ ትዕዛዞችን – ግለሰቡ ከሳሽም ይሁን ተከሳሽ – እና ሌሎችን የፍርድ ቤት ትዕዛዞች ወይም እንደ የሙከራ ጊዜ፣ የልጅ ድጋፍ ግዴታዎች ወይም ፍርድ ቤት የመቅረብ ትዕዛዞች አይነት በሂደት ላይ ያሉ ህጋዊ ጉዳዮች ያሉ ከሆነ የኢ.ኤ ቤተሰብ መረጃዎችን ለመጠለያና ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ ማቅረብ አለባቸው። ያልተዘጋን ማዘዣ ላለማዘጋት በቂ ምክንያት አለው ተብሎ የሚወሰደው በጠበቃ የተፈረመ፣ የጠበቃውን ቦርድ ኦፍ ባር ኦቨርሲዬር ቁጥርን (Board of Bar Overseers number) ያካተተ፣ የኢ.ኤ ቤተሰቡ ያልተዘጋውን ማዘዣ መፍታት እንደሌለበት እንደሚያምን የሚያሳይ የጠበቃ ደብዳቤ የሚያቀርብ ከሆነ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል ያልተዘጋውን ማዘዣ ላለማዘጋት በቂ ምክንያት እንዳለው ሊቆጠር ይችላል።

**ከውጪ ማደር**

ከውጭ ለማደር ፈቃድ ከሌለ ወይም በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የኢ.ኤ ቤተሰቦች በቤት አልባ መጠለያው ወይም በሆቴሉ እንዲያድሩ ይጠበቃል። የኢ.ኤ ቤተሰቦች እንደ ቤተሰብ **በድምሩ** በወር ውስጥ ለአራት ቀናት ከቤት አልባ መጠለያው ወይም ከሆቴሉ ውጪ አስፈቅደው ማደር ይችላሉ። ከታች በተገለፀው ዝርዝር መሰረት፣ የቤተሰብ አባል የሆኑ ግለሰቦችም ከተመደቡበት ውጪ ሊያድሩ ይችላሉ።

በተጠጋጋ ወይም በተበታተነ ጣቢያ በሚገኝ መጠለያ፣ ከቤት አልባ መጠለያው ውጭ ለማደር በኢ.ኤ ቤተሰብ የቀረበ ጥያቄ፣ ጥያቄው ለመላ ቤተሰብም ይሁን ለአባል ግለሰብ፣ ለቤት አልባ መጠለያ ሰራተኛ መቅረብ አለበት። ሆቴል ውስጥ፣ ከቤት ውጭ ለማደር በኢ.ኤ ቤተሰብ ወይም በአባል ግለሰብ የቀረበ ጥያቄ

የዲ.ኤች.ሲ.ዲ መደበኛ ቅፅ በመጠቀም በሆቴሉ ሰራተኛ አማካኝነት ለተባባሪ የዳይሬክተር ተወካይ ይቀርባል። የሆቴል ሰራተኛው ወዲያውኑ ጥያቄውን ወደተወካዩ ማስተላለፍና ይህን ማድረጉን ለኢ.ኤ ቤተሰብ ማሳወቅ አለበት። የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ማንነት እና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል የሚያስፈልገው መረጃ ተሳታፊዎች በሆቴሉ በር ላይ ይገኛል። ቢያንስ ከሁለት የስራ ቀናት በፊት በቅድሚያ ወይም ከቤት ውጪ ለማደር ያስፈለገበት ምክንያት ዘግይቶ የተከሰተ በመሆኑ ዘግይቶ በመጠየቅ፣ በወር ውስጥ ከ4 ያልበለጡ ሌሊቶችን ከውጭ ያሳለፈ የሆቴል የኢ.ኤ ቤተሰብ፣ ውጪ ከማደራቸው በፊት ከተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ጥያቄያቸው እንደተከለከለ ተገልፆ ካልሆነ በስተቀር፣ ይህን ህግ እንደጣሱ አይቆጠርባቸውም።

የኢ.ኤ ቤተሰብ ከመጠለያ ወይም ከሆቴል ውጭ ባለበት ጊዜ ውጪ ለማደር የሚያስገድድ ጉዳይ ቢገጥም ለሆቴል ሰራተኛ ስልክ በመደወል ጥያቄ ሊያቀርብና በተመለሰ ጊዜ ለምን ቀደም ሲል ጥያቄውን ማቅረብ እንዳልተቻለ በፅሁፍ ሊያብራራ ይችላል። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም፣ የሆቴል ሰራተኛ የኢ.ኤ ቤተሰቡን በመወከል ወዲያውኑ አግባብነት ላለው የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ፐርሶኔል ጥያቄውን በፅሁፍ ያቀርባል።

ከውጭ ለማደር የሚደረግ ጥያቄ ውጪ ከሚታደርበት ቀን ቢያንስ በሁለት የስራ ቀናት ቀደም ብሎ መደረግ አለበት። የተላከ ጥያቄ 2 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠበት እንደተፈቀደ ሊወሰድ ይችላል። ከሁለት የስራ ቀናት ያነሰ ጊዜ ሲቀር የቀረበ ከሆነ ጥያቄውን ቀደም ብሎ ሁለት የስራ ቀናት እየቀረ ማድረግ ያልተቻለበትን ምክንያት በመጥቀስ መቅረብ ያለበት ሲሆን ጥያቄው በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ሊከለከል ይችላል። ቅድሚያ የተገለፀ ፈቃድ ሳይኖራቸው ውጪ የሚያድሩ ተሳታፊዎች የተጠየቀው ላይፈቀድ እንደሚችል ግንዛቤ ይዘው መሆን አለበት። ውጪ ለማደር የቀረቡ ጥያቄዎችን በማየት ሂደት፣ በግልፅ የተቀመጠ በቂ ምንክያት ከሌለ በስተቀር ፈቃድ አይከለከልም። በእነዚህ ህጎች በተፈቀደው መሰረት እስከ አራት ቀናት ከውጪ ለማደር እንደሚፈቀድ ይጠበቃል። ባልተፈቀደ የቤተሰብ ውጪ ማደር ምክንያት ለደረሰ ህግ አለማክበር ወይም መባረር ለሚኖር የአስተዳደራዊ ይግባኝ፣ ስልጣንን ያላግባብ መጠቀምን ማየትን ጨምሮ በM.G.L. c. 30A, § 14 (7) ለተገለፁት ምክንያቶች የዲ.ኤች.ሲ.ዲ የተጠየቀውን ውጪ የማደር ጥያቄ ያላፀደቀበት ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

በቂ ምክንያት በመኖሩ ምክንያት በዲ.ኤች.ሲ.ዲ ካልተፈቀደ በስተቀር (ለምሳሌ ሰመር ካምፕ ላይ ያሉ ልጆች፣ የመቆጣጠር ስምምነቶች፣ ህክምና) ወይም በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያቶች መስፈርት መሰረት በቂ ምክንያት ኖሮ ካልሆነ በስተቀር፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል የሆነ ግለሰብ ከቤት አልባ መጠለያው ወይም ከሆቴሉ ለ2 ተከታታይ ሌሊቶች አለመኖር አይፈቀድም። በመጠለያ ውስጥ፣ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ለተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ በመጠለያ ሰራተኛ አማካኝነት መደበኛ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቅፅ በመጠቀም ይቀርባሉ። በሆቴል ውስጥ፣ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ለተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ በሆቴል ሰራተኛ አማካኝነት መደበኛ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቅፅ በመጠቀም ይቀርባሉ። እንዲፈቀድ በፅሁፍ የቀረበ ጥያቄ በ2 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠበት እንደተፈቀደ ሊወሰድ ይችላል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱንና ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

ባልተፈቀደ የግለሰብ ውጪ ማደር ምክንያት ለደረሰ ህግ አለማክበር ወይም መባረር ለሚኖር የአስተዳደራዊ ይግባኝ፣ ስልጣንን ያላግባብ መጠቀምን ማየትን ጨምሮ በM.G.L. c. 30A, § 14 (7) ለተገለፁት ምክንያቶች የዲ.ኤች.ሲ.ዲ የተጠየቀውን ውጪ የማደር ጥያቄ ያላፀደቀበት ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

የኢ.ኤ ቤተሰብ የፕሮግራሙን ህጎች እና መስፈርቶች ባለማክበራቸው ምክንያት የተጠጋጉ ወይም የተበታተኑ የጣቢያ መጠለያዎች ከውጪ ለማደር የሚቀርብን ጥያቄ ላይቀበሉ ይችላሉ።
አምስት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ተከታታይ ሌሊቶች ሙሉ ቤተሰቡ ወጪ ለማደር የሚቀርብ ጥያቄ ቅፅ ቲ.ኢ.ኤስ.አይ-1 በመጠቀም መቅረብ አለበት።

በዚህ ህግ መሰረት ውጪ ለማደር ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሙሉ ለተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ መቅረብ አለባቸው። እንደዚህ አይነት ጥያቄዎችን ለተባባሪ የዳይሬክተር ተወካይ በመላክ የሆቴል ሰራተኞች ቤተሰቦችን ሊረዷቸው የሚገባ ሲሆን የተባባሪ ዳይሬክተር ተወካይ መገኛን በተመለከተም በሆቴሉ የመረጃ ዴስክ መቀመጥ አለበት።

በ760 CMR 67. 06(6)(a)5 የበቂ ምክንያት መስፈርቶች መሰረት ላለመገኘት በቂ ምክንያት ከነበረ፣ ያልተፈቀደ ከውጪ ማደር እንደ ህግ መጣስ፣ ህግ አለማክበር ወይም የሚያስባርር ሊቆጠር አይችልም። ያለፈቃድ ውጪ በማደር በተሳታፊው የሚቀርብን በቂ ምክንያት በማየት ሂደት፣ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ውጪ ለማደር ፈቃድ ለመጠየቅ የተደረጉ የተመዘገቡ ጥረቶችንና ውጪ የታደረባቸውን ሌሊቶች ብዛት ጨምሮ ሁሉንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል።

ሙሉ ቤተሰቡ ቢያንስ ለ48 ሰዓታት እና ለሁለት ተከታታይ ሌሊቶች ጠፍቶ ለሁለት ተከታታይ ሌሊቶች ለመጥፋት ያስገደዳቸውን በቂ ምክንያት ለማብራራት

በጠፉት የመጀመሪያ ቀን የምሽት ገደብ ከማለፉ በፊት ለሆቴሉ ወይም ለመጠለያው ወይም ለተባባሪ ዳይሬክተር ተወካይ ሳይደውሉ ቀርተው ካልሆነ በስተቀር፣ በተጠረጠሩበት ጥሎ መጥፋት ምክንያት ቤተሰብ ከሆቴል ወይም መጠለያ ውጪ እንዲሆኑ ሊዘጋባቸው አይችልም። ዲፓርትምንቱ የቀረበውን በቂ ምክንያት በጊዜው ለማረጋገጥ ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን ማረጋገጫው በጊዜ የማይቀርብ ከሆነ ማባረሪያ መባረርን ሊያሳውቅ ይችላል። ያልተፈቀደ ውጪ ማደር ለፈፀመው ቤተሰብ ዩኒት የማይኖረው ከሆነ፣ ተሳታፊው ተመልሶ ለመግባት ለምደባ ቢመጣ፣ በ760 CMR 67.09 (2) (b) 3 መሰረት ወደ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቢሮ በስራ ሰዓት በመመለስ ጠይቀው አዲስ ምደባ የማግኘት እድል እንዳላቸው የመጠለያ ወይም የሆቴል አስተዳዳሪ ይገልፁላቸዋል። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲከሰት፣ የመጠለያ ወይም የሆቴል አስተዳደር ተሳታፊው የተመለሱበትን ቀንና ሰዓት ያሳውቃሉ።

**የግል ንብረቶች እና የክፍል ንፅህና**

በተበታተነ ጣቢያና በሆቴል ያሉትን ጨምሮ የኢ.ኤ ቤተሰብ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ከሁለት ትልልቅ (30-ጋሎን) ሻንጣዎች በላይ የሆኑ የግል ንብረቶችን ሊይዝ አይችልም። ከሚፈቀደው በላይ የሆነ ንብረት ይዘው ለመጡ ቤተሰቦች፣ በሰው እስከ አንድ ተጨማሪ ትልቅ (30-ጋሎን) ሻንጣ፣ አናም ትርፍ ይዞታቸውን ለጊዜው የሚያስቀምጡበት ቦታ የሌላቸው ከሆነ፣ አማራጭ የማስቀመጫ መንገዶች ተገልፆላቸው ሰባት ቀናት ይሰጣቸዋል፣ ወይም በ 760 CMR 67. 06(6)(a)5 በተገለፀው መሰረት በቂ ምክንያት ሲኖርና ከተባባሪ ዳይሬክተር ተወካይ በፅሁፍ ፈቃድ ሲሰጥ፣ ትርፍ እቃዎችን ለማስወገድ ምክንያታዊ የሆነ ረጅም ጊዜ (ሁሉንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት) ሊሰጣቸው ይችላል። የሚፈቀደውን የግል ይዞታ ለማስቀመጥ የሚሆን በቂ ቦታ ሆቴል በማያቀርብበት ጊዜ፣ በተባባሪ ዳይሬክተር ተወካይ ፈቃድ ቤተሰብ ማስቀመጫ ዩኒት(ቶች)ን ሊያቀርብ ይችላል። ማንኛውንም የግል ንብረቶችን ወይም እቃዎችን ማስቀመት፣ ማስቀመጫ ዩኒቶችንና በመጀመሪያዎቹ ሰባት ቀናት የመጠለያ ቆይታቸው የሚይዙትን ትርፍ እቃ ጨምሮ፣ ሁሉም የግዛትና የአካባቢ የንፅህናና የእሳት ኮዶች ይመለከቷቸዋል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ የይዞት መጠኑን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ ዲ ሚኒመስ (ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

ተሳታፊዎች ክፍላቸውን በንፅህናና በተስተካከለ መልኩ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ፍተሻ የተደረገው የመፈተሽ ህግን ተከትሎ ካልሆነ ወይም በ760 CMR 67. 06(6)(a)5 መሰረት ተሳታፊው በእለቱ በቂ ምክንያት ያላቸው እንደሆነ ከታወቀ፣ ወይም የቤተሰብ አባል ታሞ ከሆነ፣ ልብስ ለማጠብ በዝግጅት ላይ ከሆነ፣ ወይም ንብረት እየሸከፈ ወይም እያራገፈ ከሆነ ተሳታፊው ይህን ህግ እንደጣሱ አይቆጠርባቸውም።

የኢ.ኤ ቤተሰብ ከመጠለያ በሚለቅበት ጊዜ ሁሉንም ንብረቶቹን የማስወገድ ሃላፊነት አለበት።

ከመጠለያ ወይም ከሆቴል እየቀየረ ወይም እየወጣ ያለ የኢ.ኤ ቤተሰብ ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ ቢበዛ ጥቂት የግል እቃዎችን፣ በንፅህና ተሸክፈው፣ የኢ.ኤ ቤተሰቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ወደቀጣይ መኖሪያ እስኪወስዳቸው ከመኖሪያው ውጪ በትንሽ ቦታ ላይ ሊጠብቁት ይችላሉ።

የኢ.ኤ ቤተሰብ ዩኒቱን ለቆ ከወጣ በኋላ፣ በተጠጋጋ ወይም በተበታተነ ጣቢያ ቦታዎች የተተዎ ማንኛውም እቃ ለበጎ አድራጎት ከመለገሱ ወይም ከመጣሉ በፊት ለ48 ሰዓታት ተጠቅልሎ ይቀመጣል። መጠለያዎችና ሆቴሎች ከኢ.ኤ ቤተሰብ ጋር በሚያደርጉት ስምምነት በራሳቸው ፈቃድ ከ48 ሰዓታት በላይ እቃዎችን ሊያቆዩ ይችላሉ።

**የቤት እንስሳት**

የተመዘገቡ የአገልግሎት እንስሳት ወይም በአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ድንጋጌ መሰረት የተፈቀዱ እንስሳት ካልሆኑ በስተቀር፣ ማናቸውም የቤት እንስሳት በማንኛውም ጊዜ በመጠለያው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲኖሩ አይፈቀድም። ይህ ክልከላ ጊዜያዊ ወይም ለጉብኝት የሚመጡትን የቤት እንስሳትም ይጨምራል። እንስሳቱ የአካል ጉዳትን ለማገዝ ስለመሆኑ እንዲታወቅ አግባብ ያለው ጥያቄ እስካልቀረበ ድረስ አንድ ቤተሰብ ይህን ህግ እንደጣሰ አይቆጠርበትም። አንድ እንስሳት እንዲቆይ የማይፈቀድለት መሆኑ ከተወሰነ በኋላ፣ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ በቅርብ የሚገኙ የእንስሳት ተንከባካቢ ድርጅቶችንና «የማይገድሉ» የእንስሳት መጠለያዎችን ዝርዝር በማቅረብ ቤተሰቡ በመጠለያ ምደባው ቆይታ አንስሳውን ለማቆያ ሊሰጠው ለሌላ አሳዳጊ ሊሰጠው ይችላል።

**የታዘዙ መድሃኒቶች**

የኢ.ኤ ቤተሰብ ለታዘዙ መድሃኒቶች ማስቀመጥና መቆጣጠር ሃላፊነት አለበት፣ በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያቶች መስፈርት የሚታይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ።

የታዘዙ መድሃኒቶችን ለማስቀመጥ አስተማማኝ ቦታ በኢ.ኤ ቤተሰቡ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ እነዚህን መድሃኒቶች በአስተማማኝ ቦታ ማስቀመጥ አለበት። በኢ.ኤ ቤተሰቡ ክፍል ውስጥ አስተማማኝ ቦታ የሌለ ከሆነ፣ የቤተሰቡ ጎልማሳ አባል የታዘዘው መድሃኒት ልጆች በማይደርሱበት ቦታ

ለማስቀመጥ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት። በመጠለያ ውስጠ፣ ልጆች የማይደርሱበትና ከማፅጃና መርዛማ ፈሳሾች ሩቅ የሆነ አስተማማኝ ቦታ ከሌለ፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ የተጠጋጋ ወይም የተበታተነ ጣቢያ የመጠላ ሰራተኛ አስተማማኝ የሆነ ማስቀመጫ ቦታ እንዲፈልግለት እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል።

ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን ወይም ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

***ፆታዊ ጥቃት***

በመጠለያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሌሎች ነዋሪዎችን፣ እንግዶችን፣ አገልግሎት ሰጪዎችን ወይም የመጠለያ ሰራተኞችን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ላይ ፆታዊ ጥቃት ማድረስ የተከለከለ ነው።

**ያልተፈቀደ ነገር መጠቀም**

አልኮል ወይም ሌላ ማንኛውንም ቁጥጥር የተደረገበት ንጥረ-ነገር በመጠለያው ቅጥር ግቢ ውስጥ መጠቀም ክልክል ነው።

ከኢ.ኤ ቤተሰብ ቤት የማግኘት እቅድ ጋር በሚጣረስ መንገድ፣ በመጠለያው ግቢ ውስጥ በሚኖር ማንኛውም ሰው ላይ የጤና ወይም የደህንነት አደጋ በሚያደርስ መልኩ፣ ወይም የመጠለያውን አስተዳደር በሚያውክ መልኩ ከፕሮግራም ውጪ አልኮል ወይም ቁጥጥር የተደረገበት ንጥረ-ነገር ያላግባብ መጠቀም የተከለከለ ነው።

በህክምና የታዘዘን መድሃኒት ከታዘዘበት መንገድ ውጪ መውሰድም የንጥረ-ነገር መውሰድ ተብሎ ይወሰዳል።

**ነውጠኛ ባህሪ፣ ህፃናትን መበደል ወይም ትኩረት መንፈግ**

በእራስ፣ በኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት፣ በሌሎች ነዋሪዎች፣ በእንግዶች፣ በአገልግሎት ሰጪዎች፣ ወይም የዲ.ኤች.ሲ.ዲ፣ የሆቴል ወይም የመጠለያ ሰራተኞች ላይ አደጋ የሚጋርጥ ባህሪ የተከለከለ ነው። ይህም አካላዊና ፆታዊ ፀብ፣ የመዛት ወይም የማስፈራራት ባህሪ የመሳሰሉትን ያካትታል።

በመጠለያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማንኛውም አይነት የህፃናት በደል ወይም አካላዊ ቅጣት ተቀባይነት የለውም። የመጠለያ ሰራተኛ፣ የዲ.ሲ.ኤች.ዲ ሰራተኞች እና ሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ማንኛውንም አይነት የህፃናት ብዝበዛና ትኩረት ማጣት በተመለከቱ ጊዜ ለህፃናትና ቤተሰቦች ዲፓርትምንት (ዲፓርትምነት ኦፍ ቺልድረን ኤንድ ፋሚሊስ) ማሳወቅ አለባቸው።

**ጎብኝዎች/እንግዶች**

*በመጠለያዎች ውስጥ፡-*

መጠለያው እንዳለው ቦታ (ለምሳሌ ግለሰቦች ከአገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በሚገናኙባቸው ቦታዎች)፣ ምክንያታዊ ለሆነና ለተገደበ ጊዜ፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ ከጎብኝዎች ጋር ሊገናኝ ይችላል። መጠለያዎች አግባብነት ያለውን የጉብኙት ጊዜ ሊወስኑ ይችላሉ።

የኢ.ኤ ቤተሰብ ለቤተሰቡ ጎብኚ(ዎች) ባህሪ ሃላፊ በመሆኑ፣ ጎብኝዎቹ ማንኛውንም የኢ.ኤ ፕሮግራም ወይም የመጠለያ ህግ(ጎች) ቢጥሱ የኢ.ኤ ቤተሰብ ተጠያቂ ይሆናል። በዚህ ህግ ከተፈቀደው ውጪ፣ ሌሊት የሚያድሩ ጎብኚዎች ሊኖሩ አይችሉም። በመጠለያው ውስጥ ቦታ ያለ ከሆነ፣ የተንከባካቢነት ስምምነት ወይም የዲ.ሲ.ኤፍ ጥያቄ፣ ወይም ለኢ.ኤ ቤተሰብ የተላለፈ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማቅረብ፣ ቀዳሚ ቤተሰቦቻቸው በኢ.ኤ ቤተሰብ ውስጥ የማይኖሩ ልጆች ሌሊት በማደር እንዲጎበኙ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ፈቃድ በማግኘት የመጠለያ ሰራተኛ ሊስማማ ይችላል።

ሌሊት የሚያድሩ ጎብኝዎችን በተመለከተ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች በተባባሪ ዳይረክተር ተወካይ በኩል መቅረብ አለባቸው።

መጠለያው አስቀድሞ ለማዎቅ የሚፈልገው ጊዜ ያነሰ ካልሆነ ወይም በአደጋ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ የጎብኝውን ስም ከጉብኙቱ ቢያንስ ከ24

ሰዓታት በፊት ማሳወቅ አለበት።

ጎልማሳ ጎብኝዎች ፎቶ ያለበት መታወቂያ መተውና ወደ መጠለያው ሲገቡና ሲወጡ መፈተሽ አለባቸው። የመጠለያ ሰራተኛ በአካባቢው ከሌለ በስተቀር በተበታተነ ጣቢያ የሚጎበኙ ጎብኝዎች ፎቶ ያለው መታወቂያ ማቅረብ አይጠበቅባቸው፤ ይሁንና፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ ሁሉንም ጎብኚዎች ለመስጠት ሰራተኛ ማስመዝገብ አለባቸው።

የኢ.ኤ ቤተሰብ የፕሮግራሙን ህጎች እና መስፈርቶች ባለማክበራቸው ምክንያት መጠለያዎች ጎብኝዎችን ላይቀበሉ ይችላሉ።

*በሆቴሎች ውስጥ፡-*

በዚህ ህግ የሚፈቀድላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም የሌላ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት ካልሆኑ በስተቀር በሆቴል ክፍል ውስጥ ጎብኝዎች እንዲኖሩ አይፈቀድም። ሆቴሉ እንግዳ እያለውም ሆነ ሳይኖረው በሆቴሉ አስተዳደር በሚፈቀዱ የጋራ መጠቀሚያ አካባቢዎች ልክ ሌሎች ኢ.ኤ ያልሆኑ የሆቴሉ እንግዶች በሚስተናገዱበት መልኩ የኢ.ኤ ቤተሰብ ጎብኚዎች እንዲገለገሉ ይፈቀድላቸዋል። ለሆቴል ሰራተኛ ቅድሚያ በማሳወቅ የኢ.ኤ የቤተሰብ አባልን ለማገዝ ንብረት መቀበል ወይም መስጠት የጎብኝዎች ወይም የእንግዶች ህግን መጣስ አይሆንም።

ሆቴል ውስጥ የተመደበ የኢ.ኤ ቤተሰብ በተመሳሳይ ሆቴል ውስጥ የተመደቡ ሌሎች የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት ምክንያታዊ ለሆነና ለተወሰነ ጊዜ ሊጎበኙት ይችላል፤ የቤተሰብ አባላት ብዛት ከ6 በላይ ሳይሆን 6 የኢ.ኤ ተሳታፊዎች በአንድ ጊዜ በሆቴሉ ውስጥ ካልተገኙ በስተቀር። የቤተሰብ ብዛት ከ6 በሚያልፍበት ጊዜ፣ ከ6 የተረፉት የቤተሰብ አባላት ዩኒት ውሰጥ ሊቆዩ የሚችሉ ሲሆን ነገር ግን እንግዶች ክፍሉ ውስጥ ሊቆዩ የሚችሉት በአንድ ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የሚኖረው የሰው ብዛት 6 ወይም ከዚያ በታች የሚሆን ከሆነ ነው።

የልጅ እንክብካቤ በሌለበት ሁኔታ፣ ከ16 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ጉብኝት ሊያደርጉ የሚችሉት ከቤተሰባቸው ውስጥ ጎልማሳ ሰው አብሮ ሲኖር ወይም የቤተሰብ አባል የሆነ ጎልማሳ ሰው በግቢው ውስጥ ያለ ከሆነና በሌለላኛው የኢ.ኤ ቤተሰብ፣ በልጆች ስልክ ወይም በልጅ የጥሪ ድምፅ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው።
በሆቴሉ ክፍል ውስጥ ቦታ ያለ ከሆነ፣ የተንከባካቢነት ስምምነት ወይም የዲ.ሲ.ኤፍ ጥያቄ፣ ወይም ለኢ.ኤ ቤተሰብ የተላለፈ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማቅረብ፣ ቀዳሚ ቤተሰቦቻቸው በኢ.ኤ ቤተሰብ ውስጥ የማይኖሩ ልጆች ሌሊት በማደር እንዲጎበኙ የተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ሊፈቅዱ ይችላል።

ጎብኝዎች የኢ.ኤ ቤተሰብ ሲጎበኙ ሁሉንም የኢ.ኤ ፕሮግራም ህጎች ማክበር አለባቸው።

አንድ 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው(ናት) ልጅ የሌሎች በተመሳሳይ ሆቴል የተመደቡ የኢ.ኤ ቤተሰቦችን በሆቴሉ የጋራ መገልገያዎች ሊጎበኝ (ልትጎበኝ) የሚችለው(የምትችለው) ለእራሱ/ሷ የልጅ እንክብካቤ እንደሚያደርግ(እንደምታደርግ) የተፈቀደለት(ላት) ከሆነ ወይም የልጁ(ጅቷ) የቤተሰብ አባላት በሆቴል ምድር ያሉና በአጭር ጊዜ በስልክ ወይም በልጅ ጥሪ ሊገኙ የሚችሉ ከሆነ ብቻ ነው።

በኢ.ኤ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ ጎልማሳ አባላት በቤታአው ውስጥ የሚገኙ ልጆችን ጤናና ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነታቸው የማይቀንስ ሲሆን ልጆች የሌሎችን የኢ.ኤ ቤተሰብ መጎብኘት ያለባቸው ስለመሆኑ ጥንቃቄ የተሞላበት ውሳኔ መወሰን አለባቸው።

ሆቴሎች ውስጥ፣ የሆቴል ሰራተኛ የኢ.ኤ ቤተሰብ ቤተሰብን በግልባጭ በማሳወቅ ለተባባሪ ዳይሬክተሩ ተወካይ ለሚያቀርበው የፅሁፍ መጠየቂያ፣ እነዚህን ህጎች ቀደም ሲል የጣሰ ከሆነ፣ አንድ የኢ.ኤ ቤተሰብ እንዳይጎበኝ ወይም እንግዳ እንዳይሆን ምክንያታዊ የሆነ የግል ውሳኔ ይኖረዋል። ማንኛውም የጉብኘት ክልከላ እንደጥፋቱ አይነት ምክንያታዊ ለሆነ ጊዜ መሆንና ክልከላው የተደረገበት ምክንያት በፅሁፍ ተገልፆ መሆን አለበት። እንደዚህ አይነት የጉብኝት ክልከላ ስልጣን ምክንያታዊነቱን ይህን ህግ በመጣስ ምክንያት ለደረሰ ህግ አለማክበር ወይም መባረር አስተዳደራዊ የይግባኝ ጥያቄ በማቅረብ መቃዎም ይቻላል።

በሚከተሉት ምክንያቶች የሆቴል ሰራተኛ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮች ወይም የሌሎች ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር የሚሰሩ የግዛት

ኤጀንሲዎች ሰራተኞች ጉብኙቱን ሊያቋርጡት ይችላሉ፦ (ሀ) በአስተናጋጅ ዩኒት ውስጥ የሚከናወኑት ተግባራት የሌሎችን የሆቴል እንግዶች ወይም ሰራተኞች ፀጥታ የሚያደፈርስ ሲሆን፤ (ለ) በአስተናጋጅ ዩኒት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ለአስተናጋጁ፣ ለእንግዳ፣ ለየትኛውም ቤተሰብ አባላት፣ በሆቴል ለተመደበ ሌላ የኢ.ኤ ቤተሰብ፣ ለሌላ የሆቴል እንግዳ፣ ለሆቴል ሰራተኞች፣ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኞች፣ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኮንትራክተሮች ወይም ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር ለሚሰሩ ሌሎች የግዛት ኮንትራክተሮች ሰራተኞች ጤናና ደህንነት አስጊ ሲሆን፤ (ሐ) በአስተናጋጅ ዩኒቱ ውስጥ የኢ.ኤ ህጎችን የሚሸራርፉ አንቅስቃሴዎች ሲኖሩ። የተፈቀደ የልጅ እንክብካቤ ከሌለ ወይም በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያቶች መስፈርት መሰረት በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ጎብኝዎች ከምሽት ገደብ ባለማለፍና ከ8 ኤ.ኤም በፊት ባለመምጣት ህግ ማክበር አለባቸው።

*በቂ ምክንያት፦*

ያልተፈቀደላቸው ጎብኝዎችን ማስተናገድ በ760 CMR 67.06(6)(a)5. የበቂ ምክንያት መስፈርት መሰረት ምክንያት ሊቀርብ ይችላል። አንድ ተሳታፊ ያልተፈቀደላቸውን እንግዳ በማስተናገድ በቂ ምክንያት ሲያቀርብ፣ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ለጎብኚው ፈቃድ ለማግኘት የተደረጉ የተመዘገቡ መረጃዎችን እና ጎብኚው የኢ.ኤ ቤተሰብ ሊያግዝ ያስፈለገባቸውና የኢ.ኤ ቤተሰብ አባላት ሊሰራቸው የማይችሉ ነገሮችን ጨምሮ ማንኛውንም ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባል። ተደጋጋሚ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰዓቱን ወይም ቦታውን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው መሰረት፣ *ዲ ሚኒመስ*(ጥቃቅን) የህግ ጥሰቶች እንደ ህግ አለማክበር ወይም ማባረሪያ አይቆጠሩም።

**የጦር መሳሪያዎች**

በመጠለያ ግቢ ውስጥ የጦር መሳሪያ መያዝም ሆነ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው።

**ጠቃሚ፦**

*የቤት ህጎች፦*

የቤት ውስጥ ህጎች እነዚህን የተመሳሳይ ህጎች፣ የኢ.ኤ ስታቱት ወይም ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች ህጎችን የማይጥሱ እስከሆነ ድረስ፣ እንደ የማፅዳት ተራ፣ የማብሰል ግዴታዎች፣ የእረብሻ ልክ፣ ቴሌቪዥን የሚታይበት ጊዜ፣ የአለባበስ ስርዓት፣ የልብስ ማጠቢያ ጊዜ፣ ወይም የመኪና ማቆሚያ ፍላጎቶች አይነት በመጠለያው ውስጥ የሚከናወኑ የዕለት-ተዕለት እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ የቤት ውስጥ ህጎች እንዳይወጣ የትኛውም የእነዚህ የተመሳሳይ ህጎች አይገድቡም።

ነገር ግን፣ የሆቴል ወይም የመጠለያ ህጎችን መሸራረፍ በ760 CMR 67.06(5)(a)4 በተገለፀው መሰረት ህግ አለማክበር ወይም ከኢ.ኤ ተጠቃሚነት መባረር የሚያስከትል አይነት ህግ ጥሰት ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። የቤት ውስጥ ህጎችን አለማክበር መዘዋወር፣ የውስጥ ማስጠንቀቂያ፣ ወይም እንደ የቴሌቪዥን ሰዓት ገደብ አይነት የቤት ጥቅማጥቅሞችን ማጣት ሊያስከትል የሚችል ሲሆን፣ ተደጋጋሚ የቤት ውስጥ ጥሰት የሚኖር ከሆነ፣ የኢ.ኤ ቤተሰብ ቤት የማግኘት እቅዱን እንደገና በመከለስ የቤት ህጎችን ማክበር ቅድመ-ሁኔታ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል። የቤት ውስጥ ህጎች የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ግምገማ ወይም ፈቃድ ሊጠየቅባቸው ይችላል።

*እንደ ስነ-ምግባር ጉድለት የማይቆጠሩ የህግ ጥሰቶች፦*

760 CMR 67.05 (e) ውስጥ በይበልጥ እንደተዘረዘረው፣ የተጠረጠሩ የህግ ጥሰቶች እና ቤት የማግኘቱን እቅድ የሚመለከቱ ውሎችን በማዘጋጀቱ ሂደት አለመሳተፍ ወይም አለመተባበር፣ እነዚህ ነገሮች ከተከሰቱበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት (6) ወራት ውስጥ ሊፋቁ የሚችሉ ሲሆን ይህም የሚሆነው፣ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ እነዚህን ህጎች በመጣስ ወይም የቤት ማግኘት እቅዱን መስፈርቶች በተመለከተ ምንም አይነት የህግ አለማክበር ወይም የመባረር ክስተት ካልነበረ እና ለጤናና ለደህንነት አስጊ የሆኑ ባህሪያት ካልነበሩ ወይም ወዲያውኑ ሊያስባርሩ የሚችሉ ባህሪያት በመከሰታቸው ህግ አለማክበር ወይም የመባረር ማስታወቂያ ያልወጣ ከሆነ ነው። በዲ.ኤች.ሲ.ዲ ይግባኝ ሰሚ ኦፊሰር እንዳልተፈፀሙ የተረጋገጡ የህግ ጥሰቶች በቀጥታ የህግ አለማክበርና የመባረር ማሳወቂያዎች እንደተፈፀሙ ሆነው የማይጠቀሱ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን የስድስት ወር ገደብ አይጠብቁም።

*ቅፆችን መጠቀም፦*

**የኢ.ኤ ቤተሰብ እንደተመደበ በተረጋገጠ ጊዜ የቤት አልባ አስተባባሪዎች የተመሳሳይ መጠለያ ፕሮግራም ህጎችን ቅጂ ለኢ.ኤ ቤተሰብ መስጠት አለባቸው።**

*መጠለያዎች የተመሳሳይ መጠለያ ህጎችን ጥሰት ሪፖርት ለማድረግ የተመሳሳይ መጠለያ ህጎች ጥሰት ቅጽ፣* USR-1 *ይጠቀማሉ። ሆቴሎች የተመሳሳይ መጠለያ ህጎችን ጥሰት ሪፖርት ለማድረግ* HM-IR1 *ይጠቀማሉ። በቅፁ ላይ የህግ ጥሰት ቁጥሮች ለማገናዘቢያ የቀረቡ ከመሆናቸው ባለፈ በትክክል የተከሰቱትን*

ጥሰቶች የማይገልፁ ናቸው። አንድ ክስተት በርካታ ህጎችን የሚጥስ ሆኖ ሲገኝ፣ የመጠለያና የሆቴል ሰራተኞች አንድ ቅፅ በመጠቀም ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች ለመጠለያ ከቅፅ USR-1 እና ለሆቴል ከቅፅ HM-IR-1 ላይ መምረጥ አለባቸው።

*አጠቃላይ ይዘቶች፦*

1. የእነዚህ ህጎች ግልባጭ፣ የኢ.ኤ የልጅ እንክብካቤ ቅጾችና መመሪያዎች፣ ቲ.ኢ.ኤስ.አይ-1s፣ ADA ምክንያታዊ መስተንግዶ መጠየቂያ ቅፅ እና የኢ.ኤ ከውጪ ለማደር መጠየቂያ ቅጽ በእንግሊዝኛና ህጉ እንዲተረጎሙ በሚያስገድዳቸው ቋንቋዎች ተተርጉሞ ከሆቴሉ የእንግዳ መቀበያ በር እና ከመጠለያው የአስተዳደር ቢሮ የሚገኙ ይሆናል። በተጨማሪም፣ በሆቴሎች የእንግዳ መቀበያ ክፍልና በመጠለያዎች ውስጥ የአስተዳደር ቢሮ የልጅ እንክብካቤ የማመሽት ቅፆች ለማን እንደሚሰጡና ሌሎች ጥያቄዎችን በተመለከተ መረጃ መስጠት፣ ያን ሰው እንዴት ማግኘት እንደሚቻልና የቀረበ ጥያቄ ያለበትን ሁኔታ በተመለከተ መረጃ መስጠት አለባቸው። ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ፣ ሌሎች የግዛት ኤጀንሲዎች፣ የማህበራዊ አገልግሎት እና የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም የህግ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የኢ.ኤ ተሳታፊዎች ለሚያደርጉት ግንኙነት ሆቴሎች ከክፍያ ነፃ የሆነ የፋክስ አገልግሎት መስጠት አለባቸው።
2. አንድ ሆቴል ወይም መጠለያ የእነዚህን ህጎችና ቅፆች ቅጂ ህጉ በሚጠይቀው ቋንቋ ለተሳታፊ ባያዘጋጅና ባያቀርብ፣ ተሳታፊው ወደ ኢ.ኤ ፕሮግራም ሲገባ የህጎችን ግልባጭ ህጉ በሚያስገድደው ቋንቋ ካልቀረበለት ወይም በጥፋት ከመጠየቁ በፊት በምደባ ቦታው ምንም እንደዚህ አይነት ትርጉም አግኝቶ ካልሆነ፣ ህግ ትሶ ለመከራከሪያ ሊጠቀምበት ይችላል።

3. አንድ ተሳታፊ የሌላ የኢ.ኤ ቤተሰብ አባል በሚያሳየው ባህሪ ወይም ቸልተኝነት ላይ ምንም ቁጥጥር ማድረግ የማይችል እንደሆነ ለማስረዳት ከቻለ በሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች የስነ-ስርዓት ቅጣቱ ላይፈፀምበት ይችላል፦
   ሀ. እንደዚህ አይነቱን የቤተሰብ አባላት ወዲያውኑ ከቤተሰብ አባልነት ያስወገደ ከሆነ፤ እና
   ለ. የቀደመው የቤተሰብ አባል የኢ.ኤ ቤተሰቦች በተመደቡበት ማንኛውም የመጠለያ ወይም የሆቴል ቦታ እንዳይመለስ ለማድረግ ምክንያታዊ የሆኑ ርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው የሚገልፅ መስፈርት በተሳታፊውና በኃልማሳ የቤተሰብ አባል የቤት ማግኘት እቅዳቸውን ካሻሻሉ ማለትም አስፈላጊ ከሆነ መመለስን መከልከል፣ በM.G.L. c. 209A መሰረት እርሱን/ሷን በመተካት ያላግባብ የመጠቀም ትዕዛዝን ማስተናገድና በንቃት መተግበር፣ በM.G.L. c. 266, § 120 መሰረት በእንደዚህ አይነት የቤተሰብ አባል ላይ የ«ማለፍ እገዳ» ለማውጣትና በንቃት ለመተግበር ወይም በM.G.L. c. 258E መሰረት የፀረ-ማስፈራራት ትዕዛዝ ለማውጣት የመጠለያና የሆቴል አስተዳደር የሚያደርገውን ጥረት መደገፍ እና የመሳሰሉትን ካደረጉ።

4. በእነዚህ ህጎች ውስጥ «በቂ ምክንያተት» ሲባል ለበቂ ምክንያት መነሻ የሚሆኑ ሌሎች መነሻዎች ካልተጠቀሱ በስተቀር በ 760 CMR 67.06(6)(a)5 የተብራሩት አይነት ማለት ነው።

5. የኢ.ኤ አመልካቾችና ተሳታፊዎች ለሚያደርጓቸው ግንኙነቶች በሙሉ ህጉ በሚፈልገው መሰረት ዲ.ኤች.ሲ.ዲ የቋንቋ ድጋፍ ይሰጣል። የእንግሊዝኛውና የተተረጎመው የሰነድ ክፍሎች የማይጣጣሙ መልዕክቶችን በያዙ ጊዜ፣ የእንግሊዝኛው አገላለፅ የሚወሰድ ሲሆን፣ ትክክለኛ ባልሆነ ትርጉም መነሻነት ለተከሰተ ባህሪ የኢ.ኤ ቤተሰብ ተጠያቂ እንደማይሆን ማንኛውም ከእንግሊዝኛ የተደረገ ትርጓሜ ማመልከት አለበት።

6. ዲ.ኤች.ሲ.ዲ እና የኢ.ኤ መጠለያ አቅራቢዎች፣ ሆቴሎችን ጨምሮ፣ በአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካዊያን ድንጋጌ (Americans with Disabilities Act (ኤ.ዲ.ኤ)) እና መድሎን ለመከላከልና ብቃት ላላቸው የአካል ጉዳተኞች ሊያገለግሉ የሚችሉ የተወሰኑ ምክንያታዊ አቅርቦቶችንና ለውጦችን እንዲያደርጉ በሚጠይቁ ተያያዥ ህቶች ጥላ ስር ናቸው። የአካል ጉዳተኛ በመሆንዎ ምክንያት ከእነዚህ ህጎች ውስጥ የትኛውንም ህግ ቢሆን ለማክበር ችግር ከገጠመዎ፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ኤ.ዲ.ኤ ምክንያታዊ አቅርቦት መጠየቂያ ቅጽ በመሙላትና የህክምና መረጃዎችን በማስደገፍ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ በመላክ ምክንያታዊ የሆነ አቅርቦት ወይም ለውጥ ሊጠይቁ ይችላሉ።